# የእንግሊዝኛ ትምህርት የቤት ሥራ ሁኔታ በአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አጭር ቅኝት

ዓርጌ ወሌ

## 1. መግቢያ

በአጠቃላይ ሲታይ የትምህርት ቤቶቻችን ሁኔታ አሳሳቢ ድክመቶች እንዳሉት በሌሎች ጽሁፎች ተወስቷል::* ከእነዚህ ድክመቶች አንዱ ተማሪዎች ተገቢ የቤት ሥራ አገኝተው፤ የቤት ሥራውን በሚገባ ሞክረው፤ ከዚያም የሰሩት በጥንቃቄ ታርሞ የሥራቸውን ውጤት ለማየትና ለወደፊቱም ለማሻሻል የሚችሉበት ሁኔታ አለመሟላቱ ነው::

የትምህርት ጥናትና ምርምር ተቋም የቤት ሥራን ችግር በማስመልከት የመስክ አጭር ቅኝት ለማድረግ የተነሳሳበትም ምክንያት ይኸው ነው:: በዚህ ጽሁፍ በአጭሩ የሚቀርቡት የቅኝቱ ውጤት የመንደርደሪያ አሳቦች የሚከተሉት ናቸው::

2. ዓላማ – በእንግሊዝኛ ትምህርት አሰጣጥ ረገድ በአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

/1/ የቤት ሥራ ምን ያህል ጥቅም ላይ ውሏል?
/2/ የቤት ሥራን በሚመለከት ያሉት ዋና ዋና ችግሮች ምንድናቸው?
/3/ በተራ ቁጥር/2/ የሚጠቀሱትን ችግሮች ለመፍታት መምህራን ምን ዓይነት ዘዴዎች ይጠቀማሉ?

---

* ትምህርት ሚኒስቴር /አ.አ.አ/ 1983 የኢትዮጵያ ትምህርት ጥናታዊ ግምገማንና

Tekeste Negash (1990). Crisis of Ethiopian Education Some Implications for Nation Building UPPSAL Reports of Education, 29, Appsala Sweden.

3. <u>ጠቀሜታ</u> – በአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የእንግሊዝና ትምህርትን በሚመለከት የሚሰጥ የቤት ሥራ እንዲጠናከር በአሁኑ ጊዜ ያለው ችግር በጥራት መታወቅ አለበት፡፡ በተለይ ለኢትዮጵያውያን እንግሊዝና የባዕድ /የውጭ/ ቋንቋ በመሆኑና አስቸጋሪም ሊሆን ስለሚችል ትኩረት ያሻዋል፡፡ ከዚሁ ጋር አብሮ መታየት ያለበት የእንግሊዝና ቋንቋ ለከፍተኛ ትምህርት መግቢያና ከገቡም በኋላ ትምህርቱን ለመከታተያ አስፈላጊ ትምህርት መሆኑ ነው፡፡

4. <u>የጥናቱ መረጃ አሰባሰብ</u> –ጥናቱ የተመሰረተው በመጠይቅ ላይ ነው፡፡ መጠይቁ 15 ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን የአብዛኛዎቹ ጥያቄዎች መልስ በምርጫ መልክ የቀረበ ነበር፡፡ ለተወሰኑ ጥያቄዎች መልስ ክፍት ቦታ ተተቶ ነበር፡፡ ጥያቄዎቹ ስለቤት ሥራ መጠን፣ ተማሪዎች የቤት ሥራን ስለመስራታቸው፣ ስለአስተራረም ዘዴና ስለመሳሰሉት ነበሩ፡፡

5. <u>የጥናቱ ተሳታፊዎች</u> – ጥናቱ ያተኮረው ለጊዜው ለተጠቃሚ አመቺ ሆነው በተገኙ በአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ከጥናቱ የሚገኘው ውጤት የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ይወክላል ለማለት አያስደፍርም፡፡ በጥናቱ የተካተቱት ትምህርት ቤቶች ሁኔታ እነሱን የመሳሰሉትን ትምህርት ቤቶች ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን ይገልጻል የሚል እምነት አለ፡፡

ጥናቱ የ9ኛና የ11ኛ ክፍል እንግሊዝና መምህራን በፈቃደኝነት በሞሉት መጠይቅ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ከ9ኛ – 12ኛ ክፍል እንግሊዝና የሚያስተምሩትን መምህራን በሙሉ ለመጠየቅ አቅም አልፈቀደም፡፡ ስለዚህ የተወሰደው አማራጭ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ አዲስ በመሆናቸውና ለየት ስለሚሉ በተጨማሪም የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃን ትምህርት ያገባደዱ ስለሆኑ ለየት ስለሚሉ በሁለቱ ክፍሎች ላይ ትኩረት ማድረግ ነው፡፡

6. የቅንቀ ገንትና አጫጭር አበሪ አስተያየቶች

ወደ ቅንቀ ገንት በቀጥታ ከመገባታችን በፊት ለአተረጓጕም እንዲረዳ ወለስ ሰጪ መምህራንን በሚመለከት አጭር መገለጫ እንሰጣለን፡፡

7. የመለስ ሰጪ መምህራን አጭር መገለጫ

በጥናቱ የተካተፉት በጠቅላላ 56 መምህራን ናቸው፡፡ ዝርዝራን በሠንጠረዥ /1/ እና /2/ ይመልከቱ፡፡

ሠንጠረዥ 1

የመለስ ሰጪዎች ብዛት በትምህርት ቤትና በሚያስተምሩበት ክፍል ደረጃ

| ትምህርት ቤት | መምህራኑ የሚያስተምሩበት ክፍል | |
|---|---|---|
| | 9ኛ | 11ኛ |
| ቦሌ | 2 | 2 |
| የካቲት 12 | 2 | 2 |
| ከፍተኛ 12 | 2 | 2 |
| አብዮት ቅርስ | 3 | 3 |
| ምስራቅ አጠቃላይ | 3 | 3 |
| ወይንሻ ኒአለም | 3 | 3 |
| ነፋስ ስልክ | 3 | 3 |
| እንጦጦ አጠቃላይ | 2 | 2 |
| ኢትዮጵያ ትቅደም | 2 | 2 |
| ጥቁር አንበሳ | 2 | 2 |
| ዳግማዊ ሚኒሊክ | 1 | 3 |
| አዲስ ከተማ | 1 | 3 |
| ጠ ቅ ላ ላ | 26 | 30 |



ጥናቱ ከተደረገባቸው ት/ቤቶች አንዱ የከፍተኛ 12 ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሕንፃ በከፊል

ከላይ እንደተመለከተው አዲስ አበባ ውስጥ ካሉት 33 ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 12ቱ በጥናቱ ተካተዋል:: በተጨማሪም ከዓገማዊ ምኒልክና ከአዲስ ከተማ ትምህርት ቤቶች በስተቀር በሌሎቹ ከሚገኙት መምህራን መካከል ከየክፍል ደረጃው ቢያንስ ሁለት መምህራን መጠይቅን ሞልተዋል::

በጥናቱ የተካተቱት መምህራን የትምህርት ደረጃና የአገልግሎት ዘመን ደግሞ እንደሚከተለው በሠንጠረዥ /2/ ቀርቧል::

## ሠንጠረዥ 2

የመልስ ሰጪዎች የትምህርት ደረጃና የአገልግሎት ዘመን*

| የትምህርት ደረጃ | የአገልግሎት ዘመን በዓመትና ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 10 ወይም ከዚያ በታች | 11–15 | 16–20 | ከ20 በላይ |
| 12 + 3 | – | – | 1 | – |
| ዲፕሎማ | – | 1 | 4 | 10 |
| የመጀመሪያ ዲግሪ | 5 | 1 | 11 | 19 |

ሠንጠረዥ 2 እንደሚያሳየው አብዛኞቹ መልስ ሰጪዎች 29.23% / ባለ ዲግሪ ና ቸው:: በአገልግሎት ዘመን ረገድም 86.54% የሚሆኑት ከ15 ዓመት በላይ ልምድ አላቸው:: በዚህ መሠረት የሚገኘው መልስ በደህና የትምህርት ችሎታና ልምድ ላይ የተመሠረተ ነው ለማለት ይቻላል::

8. መጠይቁን ከሞሉት መምህራን የተገኙ መልሶች

በተራ ቁጥር 7 በተጠቀሱት ትምህርት ቤቶች በ9ኛ እና በ11ኛ ክፍል እንግሊዝኛ የሚያስተምሩ መምህራን ስለቤት ሥራ ሁኔታ የሰጡት መልስ በሚከተሉት 6 ንዑስ ክፍሎች በአጭሩ ቀርቧል:: ንዑስ ክፍሎቹም:

8.1 የቤት ሥራ ምን ያህል ይሰጣል?

8.2 ለቤት ሥራ የሚሰጡት ጥያቄዎች የሚገኙት ከየት ነው? ብዛታቸውስ ምን ያህል ነው? የሚሰሩት ተማሪዎች ምን ያህል ና ቸው?

8.3 የቤት ሥራውንስ የሚሰሩትና የማይሰሩት ተማሪዎች በምን ይለያሉ?

---

*4 መልስ ሰጭዎች እነዚህን መረጃዎች አላሟሉም::

8.4 መምህራን የቤት ሥራ አርማትን ለተማሪዎች የሚያስ ገነዘቡት በምን አኳኋን ነው?

8.5 የቤት ሥራ የማይሰሩ ተማሪዎች በተደጋጋሚ ሲያጋጥ ሟቸው መምህራን ምን መፍትሔ ይጠቀማሉ?

8.6 የማስተማር ክፍለ ጊዜ የሚበዛባቸው መምህራን የቤት ሥራ በሚገባ እንዲኪኬዱ ምን ቢያደርጉ ይረዳል?

8.1 <u>የቤት ሥራ ምን ያህል ይሰጣል</u>?

ከመምህሩ የተገኘው መልስ እንደሚያመለክተው ለ9ኛ ክፍልም ሆነ ለ11ኛ ክፍል ለእንግሊዝኛ ትምህርት ብዙ ጊዜ ለተማሪዎች የቤት ሥራ ይሰጣል:: /ዝርዝሩ በሠንጠረዥ 3 ይመልከቱ/ ይህ የሚያመለክተው የቤት ሥራ አለመስጠት ችግር ሆኖ ሊነሳ እንደማይችል ነው:: እንዲያውም በአንድ ጊዜ የሚሰጡት የቤት ሥራ ጥያቄዎች ብዛት በአብዛኛው ከ10 በላይ ስለሆኑ የቤት ሥራ እጦት አለ ለማለት ያስቸግራል:: ከዚህ ሁኔታ የሚወሱት ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው::

/1/ መምህራን የቤት ሥራ መስጠታቸው ተማሪዎችም የቤት ሥራ ማግኘታቸው <u>ለብቻው</u> ትምህርት በሚገባ እየተካሄደ ነው የሚያሰኝ ስሜት ሊፈጥር ይችላል:: መምህራን ተማሪዎችና ወላጆች የቤት ሥራ በመኖሩ <u>ብቻ</u> የትምህርት ሂደት ብቁ ነው ወደሚለው መደምደሚያ እንዳይደርሱ ማስታወስ ያሻል::

/2/ በአንድ የክፍል ደረጃ /ለምሳሌ በ9ኛ ክፍል/ አንዳንድ መምህራን በአንድ ጊዜ ከ16–20 ጥያቄዎችን እንሰጣለን ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ ከ6–10 ብቻ እንደሚሰጡ ተናግረዋል:: ለመሆኑ የቤት ሥራን መጠን በሚመለከት በአንድ የክፍል ደረጃ አንድ ዓይነት ትምህርት በሚያስተምሩ መምህራን መካከል መግባባት አለ?

ሠንጠረዥ 3

የቤት ሥራ የሚሰጥበት ጊዜና ብዛት

| | 9 | % | 11 | % |
|---|---|---|---|---|
| ብዙ ጊዜ | 21 | 80.77 | 26 | 86.67 |
| በመጠኑ | 3 | 11.54 | 4 | 13.33 |
| አልፎ አልፎ | 2 | 7.69 | – | – |
| መልስ መስጠት አልቻልኩም | – | – | – | – |

8.2 ለቤት ሥራ የሚሰጡት ጥያቄዎች የሚገኙት ከየት ነው? የጥያቄዎቹስ ብዛት ምን ያህል ነው?

የመምህራኑ መልስ እንደሚያመለክተው ከግማሽ በላይ የሆኑት ጥያቄዎች የሚወሰዱት ከማስተማሪያ መጽሐፍት ነው:: አንዱ ሰስተኛ ያህሉ ደግሞ ከመጽሐፍና ከመምህሩም የተውጣጡ ናቸው:: /ሠንጠረዥ 4ን ይመልከቱ/

ሠንጠረዥ 4

| | 9 | % | 11 | % |
|---|---|---|---|---|
| ከማስተማሪያ መጽሐፍ | 15 | 57.69 | 19 | 63.33 |
| በግል በማዘጋጀት | – | – | – | – |
| ከሁለቱም | 11 | 42.31 | 11 | 36.67 |

ሠንጠረዥ 4 እንደሚያሳየው ጥያቄዎቹ ከመጽሐፍትና ከመምህሩ የሚገኙ ና ቸው:: በተለይ ደግሞ ከመጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት ጥያቄዎች አጅግም የማያረኩ ሆነው መገኘታቸው የመምህራኑን የግል አስተዋጽኦ ያጎላዋል:: /በመጽሐፍ ውስጥ ስላሉት ጥያቄዎች ብቃት የተገኘውን መልስ ሠንጠረዥ 5 ውስጥ ይመልከቱ/::

## ሠንጠረዥ 5

| | 9 | % | 11 | % |
|---|---|---|---|---|
| በጣም አጥጋቢ | 3 | 11.54 | 3 | 10.00 |
| በመጠኑ አጥጋቢ | 21 | 80.77 | 18 | 60.00 |
| በጥቂቱ አጥጋቢ | 2 | 7.69 | 6 | 20.00 |
| አጥጋቢ አይደለም | – | – | 3 | 10.00 |

ለቤት ሥራ የሚሰጡትን ጥያቄዎች ዓይነት በማመልከት የተገኘው መልስ የሚከተለው ነው::

## ሠንጠረዥ 6

| | 9 | % | 11 | % |
|---|---|---|---|---|
| ቃላት መተርጎም | 2 | 7.69 | 9 | 30.00 |
| እያነበቡ ባዶ ቦታ መሙላት | 14 | 53.85 | 9 | 30.00 |
| ዐረፍተ ነገር መጻፍ | 1 | 3.85 | 4 | 13.33 |
| አንብቦ ጥያቄ መመለስ | 9 | 34.61 | 8 | 26.67 |
| አጭር ድርሰት | – | – | – | – |

በአጠቃላይ ለቤት ሥራ የሚሰጡትን ጥያቄዎች ብቃት በሚመለከት የሚከተሉት ነጥቦች ሊወሱ ይገባል::


/1/ በመጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ ጥያቄዎች አጥጋቢነታቸው የተወሰነ ይመስላል:: ሥርዓተ ትምህርት አዘጋጆች ይህን ጉዳይ በበለጠ በማጥናት ማሻሻያ መንገዶችን ሊቀይሱ ይችላሉ:: ዋናው ጉዳይ ግን የጥያቄዎቹ ጉድለት ምን እንደሆነ መለየቱ ነው:: በተጨማሪም የመጽሐፉ /Text / እና የጥያቄዎች ግንኙነት የሰመረ መሆኑ፤ እንዲሁም ተማሪዎቹ በዝቅተኛ ክፍል ማጥናት የሚገባቸውን ፅንሰ ሐሳቦች መገንዘባቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

/2/ መምህራን የተማሪዎችን የትምህርት ብቃት ወይም ችግር እያዩ ከመጽሐፉ ውጪ ለቤት ሥራ የሚሆኑ ጥያቄዎችን ቢሰጡ ይጠቅማል:: ሆኖም የሚሰጡት ጥያቄዎች ለድግግሞሽ ያህል ሳይሆን የተወሰነ ጉዳይን በልዩ ልዩ መልክ ለማጥናት የሚያስችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

መምህራን ለቤት ሥራ የሚሰጧቸው ጥያቄዎች በአብዛኛው " ባዶ ቦታ መሙላትን" እና " አንብቦ ጥያቄ መመለስን" የሚመለከቱ ናቸው:: ሁለቱም ዓይነት ጥያቄዎች በይበልጥ የሚሰጡት ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ነው:: የጥያቄዎችን ዓይነት በተመለከተ ሁለት አሳቦችን መሰንዘር ይቻላል::

/1/ ተማሪዎች በእንግሊዝኛ በጽሁፍ አሳባቸውን ለመግለጽ የሚያለማምዳቸው የቤት ሥራ የሚያገኙ አይመስሉም:: ችግሩ ከተማሪዎች ብዛትና ድርሰትን ለማረም ከሚወስደው ሰፊ ጊዜ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል:: ግን አሳብን በጽሁፍ የመግለጹ አስፈላጊነት እስከታመነበት ድረስ አጫጭርም ቢሆኑ መለማመጃዎችን መስጠት ጠቃሚ ነው::

/2/ የአንብቦ መመለስ / Comprehension / ጥያቄዎች
በ11ኛ ክፍል ደረጃ ጉልተው አይታዩም:: ይህም
የሥርዓተ ትምህርት ባለሙያዎችን አስተያየት ይጋብዛል::



ተማሪዎች በረፍት ጊዜያቸውና ፈረቃቸው ባልሆነ ጊዜ ቤተመጻሕፍትን
እንዲጠቀሙ ትምህርት ቤቶች ገፊት እናደርጋለን ይላሉ:: ይህ
ተማሪዎች የቤት ሥራቸውን እንዲያጠናቅቁ ጥሩ ድጋፍ የሚሰጥ ይመስላል::

## 8.3 የቤት ሥራ የሚሰሩት ተማሪዎች ምን ያህል ናቸው? የሚሰሩትና የማይሰሩትስ ምን ዓይነቶቹ ናቸው?

ከመምህራኑ የተገኘው መረጃ ውሱን ቢሆንም የቤት ሥራ የሚሰሩት ተማሪዎች ሁሉም አለመሆናቸው ጎልቶ ወጥቷል:: /ሠንጠረዥ 7 ይመልከቱ/::

ሠንጠረዥ 7

| | 9 | % | NR | % | 11 | % | NR | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሁሉም | 1 | 3.85 | 10 | 38.46 | 1 | 3.33 | 15 | 50.00 |
| ከግማሽ በላይ የሚሆኑት | 9 | 34.62 | – | – | 10 | 33.33 | – | – |
| ጥቂት | 6 | 23.07 | – | – | 4 | 13.33 | – | – |

የቤት ሥራ ከሚሰሩት ተማሪዎች አብዛኛዎቹ /ከ60 % በላይ የሚሆኑት/ የቤት ሥራውን የሚሰሩት በግዴየለሽነት መሆኑ ተጠቁሟል:: ከዚህም በላይ የቤት ሥራውን የሚሰሩት በአብዛኛው /ከ80 % በላይ/ ጎበዝ የሚባሉት ተማሪዎች መሆናቸውን የመምህራኑ መልስ ያሳያል::

ወንድና ሴት ተማሪዎች በቤት ሥራ በኩል ያላቸውን ትጋት በሚመለከት በ9ኛ ክፍል ምንም ያህል ልዩነት አልታየም:: በ11ኛ ክፍል ግን ሴቶች ከወንዶች የተሻለ ትጋት እንደሚያሳዩ መምህራኑ አመልክተዋል:: በአጠቃላይ ተማሪዎች ለቤት ሥራ የሚያሳዩትን ትጋት በተመለከተ የሚከተሉትን ነጥቦች መሰንዘር ይቻላል::

ሀ/ ተማሪዎች ለቤት ሥራ ያላቸውን ትጋት መምህራኑ በሚገባ ለመመዘን ያዳገታቸው ይመስላል። ይህንንም ለማለት ያነሳሳን ምን ያህሉ ተማሪዎች የቤት ሥራ እንደሚሰሩ መምህራኑ ሲጠየቁ ብዙዎቹ መልስ ሳይሰጡ መቅረታቸው ነው። /ሠንጠረዥ 7ን እንደገና ይመልከቱ።/ ምናልባት የበለጠ ትኩረት የሚደረገው የቤት ሥራ በመስጠቱ ላይ እንጂ በክትታይ ተግባሮች ላይ አይደለም ይሆናል። /ይህን ነጥብ በኋላ እንመለስበታለን/

ለ/ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የቤት ሥራ የገብር ይውጣ የሚሠሩ ከሆነ የቤት ሥራ ጠቃሚነቱ ከስምናል ማለት ነው። ትምህርት ቤቶች በፈረቃ በሚካሄዱበት ዘመን ተማሪዎች የቤት ሥራ ለመስራት ጊዜ አጡ ለማለት ያስቸግራል። ምናልባት የቤት ሥራ መስራቱ ከሚያጊኙ ሌሎች የጊዜ ማሳለፊያዎች ብሎም ከሌይ ከመገባቱ አይል ጋር ሲተያይ ከንቱ ልፋት ነው ተብሎ ይሆናል። ተማሪዎች ስለትምህርት ጥቅም በቂ በጨባጭ የሚያዩት ነገር ካላገሰራራ በስተቀር የቤት ሥራ ብቻ ሳይሆን ትምህርት ቤቱም ራሱ የሥራ–ፈት ቤት ወደመባሉ ሳይደርስ አይቀርም።

ጠ/ ጉብዝ የሆኑ ተማሪዎች የቤት ሥራ ሲሰሩ ከእነሱ ዝቅ ያለ ደረጃ ያላቸው ችሎ ማለታቸው የቤት ሥራን አንዱ መሠረታዊ ዓላማ ይቃረናል። የቤት ሥራ አንዱ መሠረታዊ ዓላማ በትምህርታቸው ደከም ያሉትን እንዲያሻሽሉ መርዳት ነው።

በገገና ክፍል ደረጃ የቤት ሥራን በሚመለከት ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች የተሻለ ትጋት ማሳየታቸው የሚያመለክተው በትምህርት ቤቶች ሁልጊዜ ብልጫ ያላቸው ወንዶች ያለመሆናቸውን ነው። ምናልባትም በቤተሰብ የሚደረገው የቅርብ ክትትልና የመምህራንም ማባበቢያ በወንድ ተማሪዎች አካባቢ በንቀት ዓይን ይታይ ይሆናል።

በአጠቃላይ የተማሪዎች የቤት ሥራ አጥጋቢ ሳለመሆኑ ብዙ መንስኤዎች ሊኖሩት ቢችሉም እንደኛው ለቤት ሥራ የሚሰጠው ማርክ ሊሆን ይችላል:: በዚህ ቅኝት እንደተገኘው የቤት ሥራ ከሲሚስተር ውጤት ውስጥ የሚይዘው ነጥብ በአብዛኛው ከ10% በታች ነው:: ይህ ነጥብ በመጠኑ ቢጨመር ተማሪዎች በትጋትም ቢሆን በቤት ሥራ ላይ የተሻለ ትጋት ሊያሳዩ ይችሉ ይሆናል:: ነጥቡ ከፍ ባለ ቁጥር ግን ጥያቄዎችን በማዘጋጀትና ማረም በኩል ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል::





ተማሪዎች የቤት ሥራ እንዲሠሩ መምህራን ክትትል እንዳያደርጉ ካወኳቸው ችግር አንዱ የተማሪዎች ብዛት ነው፡፡ ለቤት ሥራ ቁጥጥር ብቻ ሳይሆን በቤተ ሙከራም ቢሆን የተማሪዎች ብዛት አስቸጋሪ ሆኖአል፡፡


## 8.4 መምህራን የቤት ሥራ አርማትን ለተማሪዎቹ የሚያስረዱት በምን አኳኋን ነው?

ሠንጠረዥ 8 መምህራን የተማሪዎችን የቤት ሥራ የሚያርሙባቸውን ልዩ ልዩ መንገዶች ይዘረዝራል::

ሠንጠረዥ 8

| | 9 | % | 11 | % |
|---|---|---|---|---|
| የሁሉንም ደብተር አንድ ጊዜ ሰብስቦ በመውሰድ | 4 | 15.38 | 5 | 16.67 |
| በየቀኑ የተወሰኑ ደብተሮችን በመውሰድ | 3 | 11.54 | 6 | 20.00 |
| መልሱን ጥቁር ሠሌዳ ላይ በመጻፍ | 14 | 53.85 | 16 | 53.33 |
| ተማሪዎች ደብተራቸውን እንዲ ለዋወጡ በማድረግ | 3 | 11.54 | 2 | 6.67 |
| ሌላ አዚያው ክፍል ውስጥ እንዳሉ ተራ በተራ እየዞሩ ማረም | 1 | 3.84 | – | – |
| የሰሩ ተማሪዎችን ደብተር ብቻ ወስዶ ማረም | 1 | 3.84 | – | – |
| ትክክለኛው መልስ እስከሚገኝ ድረስ እያንዳንዳቸው መልሰቻ ቸውን እንዲያነቡ በማድረግ | | | 1 | 3.33 |





መምህራን የቤት ሥራ ጥያቄዎችን መልስ ለተማሪዎች በቃል ሲነገሩ ተማሪዎች መልሱን በመገልበጥ ላይ ና ቸው፡፡ ግን ተማሪዎች ይበልጥ መማር የሚችሉት በራሳ ቸው ተሳትፍ መሆኑ አይዘንጋ፡፡

ሠንጠረዥ 8 የሚከተሉትን ያመለክታል::

ሀ/ በአብዛኛው የቤት ሥራ መልስ የሚሰጠው በጥቁር ሰሌዳ ላይ ነው:: ይህ አሰራር ተማሪዎች በግል የሚያስቸግራቸውን ነጥብ ለይቶ ለማብራራት አያመችም:: አሰራሩ በውይይት ካልዳበረ የጅምላ አሰራር ይሆናል:: ከላይ በሠንጠረዡ ላይ እንደተጠቀሰው ብዙዎቹ ተማሪዎች የቤት ሥራ በለማ ይሰሩ ሰሌዳ ላይ መልስ መጻፉ ምንም ያህል ፋይዳ ላይኖረው ይችላል::

ለ/ የተወሰኑ መምህራን የተማሪዎችን ደብተር በመውሰድ እንደሚያርሙ ገልጸዋል:: ይህ በጥቅሉ ሲታይ አገባብ ያለው አቅጣጫ ነው:: ነገር ግን እርማቱ አማራጭና ትክክለኛ መልሶችን ካላመለከተ ጥቅሙ ውስን ይሆናል::

## 8.5 በተደጋጋሚ የቤት ሥራ የማይሰሩትን ተማሪዎች መምህራን ምን ያደርጉዋቸዋል?

ብርዕሱ ለተጠቀሰው ነጥብ በአብዛኛው የተሰጠው መልስ "ምክር መስጠት" የሚል ነው:: ሠንጠረዥ 9ን ይመልከቱ::

## ሠንጠረዥ 9

| | 9 | % | 11 | % |
|---|---|---|---|---|
| ያልሰሩትን ተማሪዎች በተናጠል አነጋግሮ ምክር መስጠት | 9 | 34.62 | 10 | 33.33 |
| ያልሰሩትን ተማሪዎች አንድ ላይ አነጋግሮ ምክር መስጠት | 15 | 57.69 | 13 | 43.33 |
| ወደ ትምህርት ቤቱ ዩኒት መሪ ወይም ምክትል ርዕሰ መምህር ቢሮ መላክ | 2 | 7.69 | 1 | 3.33 |
| ዝም ብሎ መተው | – | – | 2 | 6.67 |
| ሌላ በሚሰሩትና በማይሰሩት መሃከል ያለውን ልዩነት ለማጥበብ ማርክ መስጠት | | | 1 | 3.33 |
| ሳልሰሩት ለቤት ሥራ ከተመደበው ማርክ መቀነስ | – | – | 1 | 3.33 |
| ማርክ እንደሚሰጠው ስለሚያውቅ ያልሰሩበትን ምክንያት እንዲናገሩ ማድረግና አጥጋቢ ከሆነ ማለፍ | – | – | 1 | 3.33 |
| ለቤት ሥራ ማርክ በመስጠት | – | – | 1 | 3.33 |

ሠንጠረዥ 9 እንደሚያሳየው ተማሪዎች ጉድለት ሲያሳዩ ምክር መስጠቱ የሚደገፍ ነው:: ሆኖም እንዲህ ዓይነቱ ምክር በቡድን ከሚሰጥ ይልቅ በግል ቢሆን የተማሪዎቹን የግል ችግርና ሁኔታ ለማጤን የበለጠ ይረዳል:: ምክር መስጠቱ ብቻ ደግሞ በቂ አይሆንም:: የምክሩን ውጤት መገምገም ያሻል:: እዚህ ላይ መምህራን ለብቻቸው ሁሉንም መስራት ሊያስቸግራቸው ስለሚችል በትምህርት ቤቱ ውስጥ ካውንስለር ካለ የእርሱን ተሳትፎ መሻት ይጠቅማል::


## 8.6 የማስተማር ክፍለ ጊዜ የሚበዛባቸው መምህራን የቤት ሥራ በሚገባ ለማከሄድ ምን ቢያደርጉ ይሻላል?

ይህን ጉዳይ በሚመለከት የተሰጡት መልሶች በሠንጠረዥ 10 ተጠቃለዋል::

### ሠንጠረዥ 10

የማስተማር ተገባር የሚበዛባቸው መምህራን የቤት ሥራን ለማሰራት የሚቻሉበት መንገድ:

| የቤት ሥራ መስሪያ ስልት | ስልቱን የጠቆሙ መምህራን ብዛት |
|---|---|
| - የቤት ሥራን በመጠኑ ማድረግ | 5 |
| - የአንድ ክፍል ተማሪዎችን በቡድን የቤት ሥራ መስጠት | 2 |
| - የቤት ሥራ ከበብ ማቋቋም | 3 |
| - ከሴሚስተር ውጤታቸው የሚታሰብ የተወሰነ ነጥብ እንዲኖረው ማድረግ | 5 |
| - የመምህራን የማስተማር ክፍለ ጊዜ ብዛት መቀነስ | 4 |





ከፍተኛ የማስተማር ጫና ያለበት መምህር ስለተማሪው እንዲህ
የቅርብ ክትትል ማድረግ አይችልም::

## 7. ማጠቃለያ

በአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ እና የ11ኛ ክፍሎችን የእንግሊዝኛ ትምህርት በተመለከተ ከሞላ ጎደል የቤት ሥራ እንደሚሰጥ ቅኝቱ ያመለክታል:: ሆኖም ብዙዎቹ ተማሪዎች የቤት ሥራውን እንደማይሰሩ፣ ቢሰሩም በግዴለሽነት እንደሆነ ቅኝቱ በተጨማሪ ጠቁሟል:: የቤት ሥራም ለሚሰሩት መልስ የሚሰጠው በአብዛኛው በጥቁር ሰሌዳ ላይ መሆኑ ተገልጿል:: የቤት ሥራን ጨምሮ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ጉዳይ ለማሻሻል መሠረታዊ ለውጦች /ለምሳሌ ለሥራ የሚያዘጋጅ ሥልጠና ዓይነት/ ቢያስፈልግም ለጊዜው ያለውን የቤት ሥራ ድክመት ለማሻሻል የሚከተሉት ሊረዱ ይችላሉ::

- የጥያቄዎችን ቁጥር አነስተኛ ማድረግ፣
- አልፎ አልፎም ቢሆን ተማሪዎችን በግል መልሳቸውን ለክፍሉ አሰምተው አስተያየት እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ለቤት ሥራ የሚሰጠውን ማርክ እንደቤት ሥራው ክብደት ከፍ ማድረግ፣
- በአንድ ክፍል ውስጥ የሚመደበውን የተማሪ ብዛት ከ50 እንዳይበልጥ ማድረግ፣





ከ90 እስከ 120 ተማሪዎች ባሉበት ክፍል ውስጥ አንድ መምህር የእያንዳንዱን ተማሪ የትምህርት አቀባበል እንዴት ሊገመግም ይችል ይሆን?